# አሮጌ ነገርን በአዲስ ስም ያመጣች "አዲስ ነገር" አሮጌ ዘዴ መርጣ ለአዲስ ነገረኝነት ወደ ውጭ መረሸች!

**በወልደብርሃን ካሳ**

03/04/2002ዓም

የዛሬ ሁለት ዓመት መታተምና መሰራጨት የጀመረችው "አዲሰ ነገር" ጋዜጣ ህትመት መቋረጡና ዋና አዘጋጆቹም 'ለደህንነታቸው በመስጋት' አገር ጥለው ወደ ውጭ መሰደዳቸውን ሰምተናል። ይሄ ዜና ለቪኦኤ ከሰጡት ቃለ ምልልስ ተጣቅሶ ባለፈው ሳምንት በዜና ማሰራጫዎች ተዘግቧል። በዚህ ሳምንት ደግሞ 'ስራ አቆምኩ' ስላለቺው ጋዜጣና ስለኮበለሉት ጋዜጠኞች 'ሙሾ አውራጅ' ጽሁፎች እያነበብን ነው። እርግጥ 'አዲስ ነገር' በሃገራችን ሰላማዊ የፖለቲካ መድረክ ውስጥ እንደማንኛውም የሚድያ ዘርፍ ሃሳብን በነጻ በመግለጽ ለዲሞክራሲያዊ ሂደቱ አስተዋጽኦ እያበረከተች መቀጠል ሲገባት ስደትን መምረጧ ተገቢ አይደለም እላለሁ። ነገር ግን ጉዳዩን በተመለከተ በተለይ በዚህ ሳምንት እየቀረቡ ያሉ ዘገባዎች 'የሚችን አንገት  ማስረዘም' ከሚወደው ባህላችንና 'መንግስት እያሳደደኝ ነው' ለሚል ወገን ሁሉ ሙሾ በሚያወርደው 'የግል ጋዜጦች' አመል ተውጠው ዋናው እና ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ችላ ተብሎ ስላገኘሁት በጉዳዩ ዙርያ አንዳንድ ነገሮችን ለማንሳት ተገደደኩ። እርግጥ አዲስ ነገሮች 'ሊደርስብን ከታቀደው መታሰር ለመዳን ስንል መሰደድ መርጠናል' የሚሉት ክስ ስለእውነትነቱ በተጨባጭ ለማንም ማሳመን ያልቻሉትን ያክል 'የተሰደዱበት' ምክኒያት በተጨባጭ እየሆነ ባለው ነገር ና እነሱም በሰጡት ቃለምልልሰ( በተለይ ከአብይ) እንደተረዳነው ራሳቸው ፈቅደው  ያዋጣል ያሉትን ጊዜና ቦታ መርጠው  ወደ ተከተሉት የትግል መስመር መሄዳችውን ነው። ለጋዜጣዋ ቅርብ ከሆኑ ሰዎችና ወሬውን ከሰሙ ሰዎች ሁሉ የምንሰማው ነገር ደግሞ አዘጋጆቹ "ውጭ ሃገር ላሰቡት ስራና ለሰኮላርሺፕ" ሲባል በአንባቢዎች የፈጸሙት ክህደት' ስለመሆኑ ነው። የሚገርመው  ከወደ 'ነጻ' ፕሬሶች፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና አለማቀፍ የፕሬስ መብት ተሟጋቾች የምንሰማው ደግሞ 'የአሳዳጅና ተሳዳጅ' ነገር እንደሆነ ይለፈፋል። የሆነውን ለመረዳት ከጋዜጣዋ 'ድንገት' መቆምና ከአዘጋጆችዋ መኮብለል ጋር ተያይዘው እየሰማናቸው ባሉት ቁዘማዎችና የተጋነኑ የ 'እንዲህ ነበረች' ውዳሴዎች ባሻገር ጥያቄዎችን በማንሳት ጉዳዩን መመልከት ተገቢ ይመስለኛል።

በመጀመሪያ አዲስ ነገር ጋዜጣ  በሃገራችን ካሉ ሌሎች የግል ጋዜጦች በተለየ ምን አዲስ ነገር አገኛትና ነው ስራዋን ያቆመችው? ኮብላዮቹ አዘጋጆችስ እውን አገር ውስጥ እንዲነገርላቸው ና በከሃገር ውጭ ባሉ ወገኖች ዘንድ እንዲታወቅላችው የሚፈልጉት 'የነጻ ፕረስ ሰማዕትነት' ነው የሚገልጻቸው ወይስ ይህንን ድራማ በማቀናበር ውጭ ሃገር መኖሪያ ምክኒያት በመፍጠር አዚያ ባለ 'ትግል' ወይም ጥቅም ውስጥ ለመካተት የተወጠነ ሴራ? ጋዜጣዋ ከመቆምዋ ጋር ተያይዘው በአዘጋጆችዋም ሆነ በሌሎች 'አጋሮች' እየተነገሩን ያሉት እውነተኛውን ገጽታ የሚያሳዩ ወይስ አገር ጥለው ለወጡት አዘጋጆች የ 'ዞምቢነት' ምስላቸውን ደብዛ በማጥፋት የ'ሰማእትነት' ክብር ለማላበስ?  ከምንም በላይ ደግሞ በነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ላይ ክስና መታሰር ያሉና የተለመዱ ነገሮች ብቻ ሳይሆኑ እንዲያውም ብዙዎቹ እኒህንና ለሌሎች ተጨማሪ 'መሳደድ' የሚሉዋቸውን ችግሮች ተቋቁመው ስራቸውን እያከናወኑባት ባለች ሃገር አዲስ ነገሮች ሊከናወን 'ታቅዶብናል' ባሉት ክስ ሰበብ ስራ ማቆምና 'አገር ጥለው መሰደዳቸው' ተገቢ ነው? ወይስ አዲስ ነገሮች ህግ ቢተላለፉ አጥፍታችኋል የሚላቸው ወገን በህግ ፊት

ላያቆማቸው ወይም ላይከሰሱ በብቸኝነት የተገባላቸው ቃልና የጸደቀላቸው አንቀጽ ነበር? በአጭሩ 'አሳዳጁ' ማነው? ተሰሳዳጁስ? እነዚህንና ሌሎች መሰል ጥያቄዎች ስናነሳ ጉዳዩ እየተባለ ካለው ነገር ጋር ተጻራሪ መሆኑን መመልከት አይከብድም። ለማንኛውም አስተያየቴን ልቀጥል።

<u>አሳዳጁና ተሳዳጁ ማነው?</u>

ኢህአዴግ ደርግን ጥሎ አዲስ ስርዓት ከዘረጋና በኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት ከታወጀበት ከ1983 ዓም ጀምሮ ላለፉት 19 ዓመታት በ 'ድሮ ቀረ' የሚቆዝሙና አዲሱን ስርዓት በፍጹም ጽንፈኝነት የሚኮንኑ እጅግ ብዙ 'ነጻ' ፕሬስችን አይተናል። ቁጥራቸው የ'ነጻዎቹ' ያህል ባይበዛም የገዥው ፓርቲ ሃሳብን ብቻም የሚያራምዱ የመንግስትና የፓርቲ ሚድያዎችም አዲሱ ስርዓት ሃገሪቱ 'ካለፉት ስርዓቶቸ የወረሰቻቸው አስከፊ ሁኔታዎችን ለመቀየር የታቀዱ መርሃ ግብሮች አበረታች ለውጥ ያመጡ ጅምሮችና ከፍተኛ ውጤት ስለተገኘባቸው የስራ ክንውኖች በመተረክ ላይ ያጠነጠኑ ዘገባዎችና ትንታኔዎቸ ላይ ተጠምደዋል። በጥቅሉ 'የመንግስት' ወይም 'የገዥው ፓርቲ' የሚባሉት ሚድያዎች 'የተጋነነ በጎ ምስል በመስጥትና ተስፋ ሰጭ ድርጊቶች ላይ አትኩሮ በመደጋገም ወደ አሰልቺ ፕሮፓጋንዳነት የማውረድ ይምንታዘበው ነገር ነው። በተጭባጭ የተገኙ ውጤቶችንም ጭምር መከናወናቸውን ማሳመን አልቻሉም የሚል ትችት ከራሱ ከገዥው ፓርቲ ጭምር ተደጋግሞ ተሰንዝሯል። 'ነጻ' ወይም 'የግል' በሚባሉት ሚድያዎች ሲታዩ ደግሞ ጽንፈኝነት፣አሉባልተኝነትና ስም አጥፊነት 'ቋሚ ቤተኞቻቸው' ሰለመሆናቸው ሁሉም ወገን ይስማማል። ስለ 'ነጻዎቹ' ሚድያዎች ጨለምተኝነት መብዛትና የሃላፊነት ስሜት ማነስ በተመለከተ ልዩነት ያለው ልዩ ልዩ ወገኖች ጉዳዩን የሚያዩበት መነጽር መለያየትና ከሱም ጋር ተያያዥ ፍላጎቶች መኖራቸው ነው። የተለይዩና ሃሳቦች የሚያራምዱና ተቃራኒ የፖለቲካ ጎራዎችን የሚደግፉ ግን ሃላፊነት የሚሰማቸው ግለሰቦች ጽንፈኝነትንና ጨለምተኝነትን ሲያወግዙና እንዲታረም ሲውተውቱ ቢታይም በቡድኖች በኩል በተለይም በተቃዋሚ ፓርቲዎችና በዲያሰፖራ ፖለቲከኞች እንዲሁም እኩይ አጀንዳቸውን በውክልና የሚያራምዱ የውጭ ሃይሎች ድርጊቱን ገዥው ፓርቲን የመፋለሚያና አገሪቱን ማዳከሚያ ዋነኛ መሳሪያ እድርግው በመቁጠር ድርጊቱን የማጠናከር ድርሻቸው ከመጫወት አልተቆጠቡም። ኢህአዴግ መራሹ የኢትዮጵያ መንግስትም በአንድ በኩል በሃገሪቱ ለዘረጋው አዲስ የፌደራልዊ መንግስት አወቃቀርና የብዙሃን ፓርቲ ተኮር ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የመደራጀትና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ከብሄሮችና ህዝቦች መብቴ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል ከሚለው መብት ባልተናነሰ የማእዘን ድንጋይ ነው በማለት ነጻ ፕሬሶች እውን እንዲሆኑ አድርጓል። እንዲጎለብቱም ሲል ፈርጀብዙ አደገኝነታቸውን ሳይቀር በመታገስና በማቻቻል ብዙ ርቀት መጓዙ አሌ የሚባል ነገር አይደለም።ታዲያ የዚያኑ ያክል ባልተገራ ጨለምተኝነትና ማጥላላት በግለሰቦች ወይም በቡድኖች ብሎም ህዝብ ከህዝብ ጭምር የሚያነሳሱና የሚያነካኩ አደገኛ ዘገባዎች በነጻው ፕሬስ ሲዘገቡ ቾል በማለት የሚተቸውን ያክል የመንግስትና የፓርቲን ጥቅም የሚጻረሩ ዘገባዎችንና ዘጋቢዎችን 'ያዋክባል' ተብሎ በተደጋጋሚ ከመከሰስም አላመለጠም። በዚህ ጉዳይ ላይ ትንተናና ፍርድ መስጠት የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ባይሆንም አንድ የነጻ ፕሬስ ወይም ጋዜጠኛ 'መስራት አልቻልኩም' ቢል ወይም 'መንግስት ስላሳደደኝ ጠፋሁ' ብሎ አገር ጥሎ( ጥፋት ፈጽሞና ሃገር ክዶም ጭምር) ወደ ውጭ ሲጉዋዝ የሚለው ነገር እውነት ይሁንም አይሁንም መንግስትን በ'አጥፊነት' የመክሰስና የመኮነን ዘመቻ በተደገገሚ ይስተዋላል። እንዲህ አይነቱ ግብዝ ስሞታ በአለማቀፍ ተቋማት በሁሉም ነጻ ፕረሶችና በዲይስፖራ ፖለቲከኞች በስፋትና በቋሚነትየሚከወን የስራ ዘርፍ መሆኑ የፈጠረው ሰፊ ክፍተት ከተቆርቋሪነት ይልቅ የችግሩ ምንጭና አባባሽ መሆኑ ግልጽ እየሆነ ነው። ከእነዚህ ወገኖች የሚወርዱት ሙሾዎችና ውግዘቶች 'የአጥቂነት' ደረጃም ይዘው መንግስትን የሰይጣንነት ምስል ሲያላብሱ በአንጻሩ 'ተጠቂ' የተባሉ ጋዜጦችና ጋዜጠኞችን እንከንየለሽ

ያደርጉዋቸቸዋል። መንግስት ወደ ተከላካይነት ወርዶ `አልተደረገም' ቢል ወይም ቆፍጠን ብሎ `ተጨባጭ እውነቱ ሌላ መሆኑ' ቢያብራራ አሊያም ዝምታን ቢምርጥ በከሳሾቹ አይን አፍና ብእር ሁሌም `አፋኝ' ተብሎ መፈረጁ አይቀሬ ሁኗል።

በአንጻሩ `ተዋከብን ተሰደድን ' ባዮቹ ደግሞ እውነት ይኑራቸው አይኑራቸው በከሳሾቹ የደረጃ ሰንጠረዥ `መላእክት' እና `ሰማእታት' ሁነው ይመደባሉ። ተጨባጭ አውነታዎች ላይ በመመርኮዝ ስለሁኔታው ከዚህ የተለየ አቋምና መረጃ ያለው ክፍል በተለይ በከሳሾቹ በኩል የመስተናገድ እድል የለውም። `ነጻ' ፕሬሶቹና ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ እነሱ `ማጥቂያ መሳርያ' ካደረጉት `ውንጀላ' ጋር የማይጣጣም ሃሰብ ማቅረብ እንደ `መዓት' ስለሚቆጥሩት ለማስተናገድ ዝግጁ አይደሉም። በመንግስት በኩል ተሰልፎ እያለ እምርረው ሲያጣጥሉትና ሲያጠለሹት የነበረን ግለሰብ (ባለስልጣን፣ ባለሙያ፣ ጋዜጠኛ ወዘተ) ከነበረበት ቦታ በልዩ ልዩ ምክኒያት ቢለቅ ቢባረር ወይም ሃገር ለቆ ቢሄድ በቅጽበት(ዘርፎና ሃገር በድሎም ቢሆን) `መልአክ' የመደረግ ዋስተና ይሰጠዋል። እድሜ ለ'ነጻ' ፕሬሶች። ለዚህም ነው ጥቂት የማይባሉ ሰዎች `ለሃገር በመቆርቆራችን ወያኔ አያሳደደን' ብለው አገር ክደው ወደ ውጭ መሄድን እንኩዋን `ለሃገር ፍቅር' ሲሉ እንደሚያደርጉት የተቀደሰ ተግባር ሲቆጥሩት የምናየው። የአለማቀፍ ተቋማት በተለይ ከወደ ፕሬሱ በኩል ማንኛውም `አቤቱታ' በተሰማ ቁጥር ዝንፍ የማይሉ ` ሁኔታው አሳስቦናል' ፣ `መንግስት አፈናውን ያቁም' ፣'የዲሞክራሲው ነገር ተስፋ አስቆርጦናል' ወዘተ በሚሉ መግለጫዎችና ክሶች ብቻ ሳይወሰኑም `ለተሳዳጆቹ' መጠናከርያ ጉርሻና ቀለብ የመስፈር ስራም ይሰራሉ። በዚህም ክፍተት ጥቅም ለማጋበስ ሲሉ ድራማውን ያቀናበሩ `ጋዜጠኞች' የሰማእትነት ልብስ ተሰጥትዋቸው ቪዛ ግሪንካርድና የትምህርት እድል ከ`አንቱታ' ጋር አግኝተው ` ውጭ እየኖሩ እንዳሉም የሚካድ አይደለም። አብዛኞቹ `የሚድያው ሰዎች' (በግሉም ሆነ በመንግስት ሚድያ ሲሰሩ ቆይተው "ሊያስሩኝ ሲያስቡ አመለጥኩ" በሚል አገር የሚለቁት) የአለማቀፍ ተሙዋጋቾች `ፈጽሞ አትንኩዋቸው' አቋምና በጀት ሃሳብን በነጻ የማራመጃ ስርዓቱን ለማጠናከሪያነት ሳይሆን ለግል ህይወታቸው `የኑሮ ዘዴ' ሲያደርጉት በተደጋጋሚ አስተውለናል። አለማቀፍ ተቋማት ለነጻው ፕሬስ መጠናከር ጥብቅና መቆማችው ችግር ነው ወይም ነጻው ፕረስ አደገኛ ዘገባዎች ያሰራጫልና ይታፈን ባልልም የአለማቀፍ ተቋማቱ ችግሩን `ከመንግስት አፋኝነት' ጋር ብቻ አቆራኝተው መመልከታቸው ራሱ ችግሩን ኮትኩቶ እያሳደገ ያለ ነገር መሆኑ ሊሰመርበት ስለሚገባ ነው። በተለይ አሁን በ'አዲስ ነገር' አዘጋጆች የሆነው ይህ ግብዝነት የወለደውን ክፍተት በመጠቀም በእርግጠኝነት ከጎናችው እንደማይጠፉ በተማመኑበት የ'ነጻ' ፕሬሶችና የተቃዋሚ ፓርቲዎች `መሳደድ' አራጋቢነት ከአለማቀፍ ተቋማት አውጋዥነት ጋር ተደምሮ `ሰማእትነት' በማከናነብ አገር ጥለው ለወጡበት ምክኒያት `በቂ' ሽፋን እንደማይነፈጋቸው በማመን ያደረጉት ነገር መሆኑ በጉልህ ስለምናይ።

አዲስ ነገሮች በዚህ ክፍተት አትራፊ ለመሆን ወደ ውጭ እንደተፈተለኩ ይበልጥ ደግሞ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ችግር(እንደነሱ አባባል `የመንግስት ደህንነት ሊያስራቸው መዘጋጀት') አስገድዷቸው ሳይሆን የግል ጥቅም ለማሳደድ ወደ ውጭ እንደነጎዱ ለማንም ግልጽ ነው። አዘጋጆቹ ከ`አንዳንድ የዲፕሎማቲክ ምንጮች' ጋር በፈጠሩት ትስስር አንዱ ከዓመት በፊት ሌላኛውም ከወራት ቀደም ብሎ ወደ ውጭ መውጣታቸውና ትምህርት ወይም ስራ መጀመራቸው `እንደታቀደ ሰምተነዋል' ከሚሉት ያልተከናወነ ክስ በላይ ስለሄዱበት ጉዳይ አስረጂ አይደለም እንዴ? ቀድሞ የሄደው አብይ ተክለማርያም ከአመት በፊት የደህንነት ሚንስትሩ ስልክ ደውለው አስፈራርተውት እንደነበር የሚነግረን አሁን `መልቲ ሚድያ' በመጠቀም ውጭ ሁኖ ሊያፋፍመው ለወጥነው `የማንኛውም ዓይነት ትግል' ስትራቴጂ የማስፈጸሚያ ፕሮፓጋንዳ ስልት ወይስ `ከዛቻው' በኋም ከረር ያሉ ሃሳቦችና ትንተናዎችም ጭምር እሱ ከወጣ በኋላም በነጻነት ስትዘግብ የነበረች ጋዜጣን `ተሳዳጅነት' የሚገልጽ?

አይደለም ስለቅንጅትነት 'ኒዮ ደርጊስት' (አፍቃሬ ደርግ) መሆኑንም ሳይሸማቀቅ እየጠቀሰ ያመነበትን ሃሳብ ከመግለጽ ተገትቶ የማያውቀውና ጋዜጣዋ እስክትቆም ድረስ ዘገባዎቹን ስናነብለት የነበረው ታምራት ነገራ 'በተለይ እኔ በምርጫ 97 በአዲስ አበባ የቅንጅት ተመራጭ ስለነበርኩ የምታየው በተቃዋሚነት ወይም በሸብርተኝነት ነው" ሲለን ምን ማለቱ ነው? በወቅቱ ፓርላማ አንገባም በማለት 'በኃዳና ነውጥ ህገ መንግስታዊውን ስርዓት በሃይል ለመናድ አነሳስተዋል' ተብለው የተከሰሱትና በቁጥጥር ስር ውለው የነበሩት የቅንጅት ከፍተኛ አመራሮች በሃገሪቱ ህግና የሽምግልና ወግ ተዳኝተው ከተፈቱ በኋላ ብዙዎቹ ወደ ሰላማዊው የትግል መድረክ ተቀላቅለው ከአዲስ ነገር ጋዜጣ እድሜ በላይ ጊዜ ያለፈ መሆኑ አላስተዋለም እንዴ? ሌላው ቀርቶ የቀድሞው ቅንጅት አመራሮች ከእስር መፈታት በኋላ ፓርቲው ተከፋፍሎ የወራሽነት ንትርክና ጠብ በ'መንፈሱ'፣ በ'ስሙ'፣ በ'አርማው'፣ በ'ፕሮገራሙ'፣ በ'ስልቱ' ፣ በወዘተ ዙሪይ ሲጧጧፍ የተወለደችው 'አዲስ ነገር' የመሰላትን ወገን በመደገፍም ይሁን በመቃወም በፈቃዷ ስራ እስካቆመችበት ጊዜ ድረስ ሃሳብ የምታመላልስ እጅግ ንቁ ተሳታፊ አልነበረችም እንዴ? ያውም ከቀድሞው ቅንጅት አንድ 'ወራሽ' ፓርቲ አንጋፋ አባል በ "አርባ አምባሻ መላስ" አባዜ እስክትነቀፍ ድረስ።

ሌላው አስገራሚ ነገር በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አዲስ ነገርን ወይም አዘጋጆችዋን የሚተቹ ጽሁፎች ተከታትለው መውጣታቸው 'እኛን ለማሰር ዝግጅት እየተደረገ ነበር' ለሚለው ክስ እንደማስረጃ መቅረቡ ነው። የዘህ ክስ እውነትነት ለማረጋገጥ ከመክበዱም በላይ የአዲስ ነገር አዘጋጆች እነሱ በሌሎች ግለሰቦች ቡድኖች ወይም ተቋሞች ዙርያ( በተለይ በመንግስትና በገዚው ፓርቲ) ወጥና መጠነ ሰፊ ትችት ያቀርቡ እንደነበረው ሁሉ በነሱ ላይ (ያውም ጥቂት) ትችት ሲቀርብ እንደ 'አፈና' ወይም 'እስራት' የሚቆጥሩ መሆናቸውን ያሳየናል። ይህ ደግሞ ሃሳብን በነጻ ከመግለጽ መንፈስ ፈጽሞ በሚጻረር ጽንፍ ተቀምጠው እንደነበርና በዚህ ሰበብ ከሃገር ሸሽተው በመውጣት 'የሰማእትነት' ክብር ለማግኘት የሚሹ ግብዞች ያደርጋቸዋል።

ሌላው ቀርቶ በሚዘግቡት ነገር መነሻነት በማንኛውም ወገን ቢጠየቁ ወይም ጥፋተኛ ተብለው ቢታሰሩ ጉዳዩ ህግን ከመጣስና ካለመጣስ (ከመተላለፍና ካለመተላለፍ) ጋር ተይይዞ የሚታይ ወይስ ከህግ በላይ ስላለች አንዲት ጋዜጣ ወይም አዘጋጆችዋ 'እነሱንማ ፈጽሞ አትንኩብን' እንድንል ስለተፈለገ በእርግጥ በጋዜጠኞች ላይ ስለ ተነሱ ብዙ ክሶች በፍርድ ሂደት ተረጋግጠው ብይን የተሰጠባቸው (እስራተ የገንዘብ ቅጣት በነጻ መሰናበት የመሳሰሉ) ጉዳይችና በማስረጃ እጦት የተዘጉ ወይም ጉዳያቸው በምልልስ እየታየ ያሉም እንዳሉ እናውቃለን። ይህ ማለት ጋዜጣ ቆመ ወይም ሃሳብ በነጻነት መግለጽ ታፈነ የሚያስብል አይደለም። የሚያስከስስ ስራ ሰሪና ህግ ተላልፈሃል ብሎ የሚከስ ወገን ከመኖሩ በላይ ከሳሽና ተከሳሽን የሚዳኝ የፍትህ ሂደትና ህገመንግስታዊ ስርዓት መኖሩ ነው። ይህም ስላለ ይመስለኛል ጥቂት የማይባሉ ጋዜጠኞችና ጋዜጦች ከተራ ግለሰብ ወይም ተቋም ማጠልሸት እስከ 'የሃገሪቱን ህዝቦች ተቻችሎ የመኖር ባህልን ለመሸርሸርና ህዝብን በህዝብ ማነሳሳት' ተከስው በፍርድ ሂደቱ እንደየጉዳያቸው አሳማኝነት ሲታሰሩና በነጻ ሲሰናበቱ የምናየው። ብዙዎቹ በተደጋጋሚ እየታሰሩና እየተከሰሱም ጭምር የተለመደ ስራቸውን ሲያከናውኑ ይታያሉ። ታዲያ የአዲስ ነገር "በታሰበብኝ ክስ ከመታሰሬ በፊት" በሚል ተልካሻ ምክኒያት ማቆምና ሃገር ጥሎ መሄድ የፈረደበት መንግስትን 'አሳዳጅ' በማድረግ አዘጋጆችዋ "ውጭ ተኮር የኑሮ ዘዴ" መርጠው ያደረጉት ጉዞ ብቻ ከመሆን አይዘልም። በዚህ የአዲስ ነገሮች 'ትራጂኮሜዲያዊ' ድራማ 'አሳዳጅ' ገጸ ባህርያት ራሳቸው አዘጋጆቹና ኮናኝነትን ሆን ብለው የሚያራግቡት ግብዞቹ አለማቀፍ ተቋማት፣ 'ነጻ' ፕሬሶችና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲሆኑ 'ተሳዳጁ' ደግሞ መንግስት ሁኖ እናየዋለን።አሳዳጆቹም መንግስትን ከመጥቃት አልፈው የዲሞክራሲ ስርዓታችንና አጠቃላይ ሃገራችንን እያጠቁ ነው። ይህ ጉዳይ መንግስትን ለመቃወም በሚል ሰበብ በክስ የስራ ዘርፍ የተሰማሩት ዞምቢ 'ነጻ' ፕሬሶችና ዞምቢ

ተቃዋሚዎች ህቡእ አጀንዳ በውክልና ከሚያራምዱ አለማቀፍ 'የፕረስ መብት ተሟጋቾች' ጋር የልቅሶ ግንባር ፈጥረው ለየግል ፍላጎታቸው ሲሉ ስር እየሰደደ ያለውን የዲሞክራሲ ስርዓታችንና ሃገራችንን የማዳከም ስራ የሚያከናውኑበት የትግል መስክ መሆኑ በገሃድ እየታየ ነው።አዎ! በምናባዊ ግምት 'አገር ምንተዳየ' ባይ 'ዞምቢዎች' በሃገራችን እንደበዙ ስትነግረን የነበረችው ጋዜጣ የእውነተኛዎቹ ዞምቢዎች ህቡእ ምሽግ እንደነበረች አስመስክራለች።

**<u>ዞምቢዎቹ 'አርባ አምባሻ ከመላስ አንዱን መግመጥ' መርጠዋል!</u>**

አንድ ወቅት በዚች ጋዜጣ የቄሳርነት ክብር የነበራቸው ፕሮፌሰር መስፍን በቅርቡ ከዋና አዘጋጁ መስፍን ነጋሽ "ያለዎት ቀሪ ሂሳብ" በሚል ርእስ ለተጻፈባቸው የሰላ ሂስ "በሂሳብ የተሰላ ሃሳብ" በማለት ምላሽ ሲሰጡ ያሉትን አሁን ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል። አባባለቸው በዞምቢዎቹን አቅጣጫ የምትጠቁም ገላጭ አረፍተ ነገር ስለሆነች። ያኔ ፕሮፌሰሩ አዘጋጁን በሽርደዳ "አርባ አምባሻ ከመላስ አንዱን መግመጥ" እንደሚሻል በመንገር ጋዜጣዋ ከ'አርባ' አቅጣጫ 'የሚላስ' ነገር የመቀበል አባዜ እንደነበራት የውስጥ አዋቂ ምስክርነታቸው ነበር የሰጡት። አባባሉ በተለይ በጋዜጣዋ ይስተናገዱ ከነበሩ የተቃውሞ ጎራው 'የቀድሞና የዛሬ' ልዩ ልዩ ዘርፎች ብሎም ከ'አንዳንድ የዲፕሎማቲክ ምንጮች' የነበራት ንክኪ ስናስታውስ ይበልጥ ግልጽ ምስል ይሰጣል። በ'አዲስ ነገር' የሚላሱ ብዙ እምባሻዎችና ለጋዜጣዋ 'አምባሻ' የሚያልሱት ብዙ ወገኖች ስለመኖር። የ'ዲፕሎማቲክ ምንጮች' ስጋትና ፍላጎትን አጀንዳ ከመሆን አልፈው ፍጥጥ ባለ መልኩ በውጭ ሃይሎች ምልከታ ሃገራችንና ክፍለ አህጉራችንን የሚመለከቱ ጉዳዮች በጋዜጣዋ ፊቸር በስፋት ይተነተኑ ስለነበር ዳጎስ ያለው 'አምባሻ' የማን እንደነበር ለማወቅ አይከብድም። ምሳሌ ለመጥቀስ ያህልም ቻይና በኢትዮጵያና በሌሎች አፍሪካ ሃገሮች የምታካሂደው የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለሃገራችንና አጠቃላይ ለአህጉሪቱ ካለው ጠቀሜታ ሳይሆን በጉዳዩ የምእራባውያ ስጋት ብቻ ታሳቢ በማድረግና ሙሉ በሙሉ የነሱን ስሞታ በመመርኮዝ በስፋት ተተንትነዋል። የኢትዮ–ሱዳን ግንኙነት በተመለከተ በሁለቱ ሃገሮች ህዝቦችና መንግስታት መካከል ያሉ ጥብቅ ትስስሮችና ተጨባጭ የጥቅም መፈላለጎችን ከቁብ ባለመቁጠር ምእራባውያን ከሱዳን ጋር ጥልቅ ባላንጣነት እንዲኖረን ብዙ የሚማስኑበትን አጀንዳ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። 'አዲስ ነገር' ጋዜጣ አጀንዳውን በመሸከም ሱዳን ለሃገራችን የጸጥታ አደጋ ምንጭ መሆንዋንና ልንዘጋጅበት እንደሚገባ ለማሳመን ብዙ ደክማለች። ሱማሊያን በተመለከተ በጋዜጣዋ ይቀርቡ የነበሩ ተከታታይ ጽሁፎች በአመዛኙ ጉዳዩን ከውጭ ሁነው ኢትዮጵያ የፈጠረችው 'ሲኦል' እንደሆነ ለማሳመን ከሚሞክሩ ወገኖች እይታ አንጻር ነበር የምታቀርበው። ከሁሉም በላይ ይህች ጋዜጣ ከውጭ 'በሚላስ አምባሻ' ሃሳብ ማራመጃ ብቻ ሳይሆን ከባእድ ሃገር በሚመጣ ተጽእኖም ሃገሪቱን የማስቀጣት(ቢቻል መንግስት የመጣል) ህልም እንደነበራት ገና ከጅምሩ አፍ በፈታችበት HR2003 ዙርያ መስክሯል። ስራ ስትጀምር 'ሀ' ብላ ሽፋን የሰጠችው ይህ ጉዳይ የአሜሪካ ኮንግረስ በሃገራችን ላይ ማእቀብ እንዲጥል የተጋነነ ተስፋ በመሰነቅና በኢህአዴግ መንግስት ላይ የመጨረሻው መአት ወርዶ 'ከወያኔ የመገላገያ' ጊዜ አብሳሪ ስለመሆኑ በመስበክ ብዙ ደክማለች። ሰንበትበት ብሎ በመጣው "አባማማንያ" ደገሞ ግንባር ቀደም 'የቫይረሱ ተሸካሚ' በመሆን አዲስ ነገር የ"ወዮ ለመለስ" ስብከት መምራቱን ማንም አልቀደማትም። አሜሪካን ለመምራት የተመረጡት ኦባማ ለኢትዮጵያም ተርፈው 'የነበረው ሁሉ እንዳልነበር' ለማድረግ ቶሎ ወደ ተግባር እንዲገቡም ወተወተች። እንዲያውም ዋና አዘጋጁ አብይ ተክለማርያም ከወደ ኢምባሲ በኩል በተሰጠው እድል 'ሲመረጡ ለሚታደጉዋት ሃገር' ታስቦ በሚመስል 'ግብዣ' መጀመሪያ 'ልምድ ለመቅሰም' አሜሪካ ሂዶ መክረሙና አልፎም ወደ እንግሊዝ በመዝለቅ እራሱ እንደነገረን ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ "ለቁጥጥር ከባድ የሆነ የሚድያ አሰራርን በግዞት ጠያቂ ስርአቶች ውስጥ እንዴት ማቋቋም እንደሚቻል" የሚል ትምህርት እየተከታተለ የነበረና ያለ መሆኑን ለማወቅ ችለናል። በቀሪ ክንፍነት እዚህ ተቀምጠው በሃገሪቱ

የትምህርት ፖሊሲና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በመሰረተ ልማት ዝርጋታ እንቅስቃሴ፣በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችና በልዩ ልዩ ክንውኖች ዙርያ ወዋ የማጠልሸትና የማንኳዋሰስ ዘገባ በስፋት ከማሰራጭት አልቦዘኑም። ያውም እነ ቢቢሲ የሚወዱት ሃገራችንን የ'አስከፊ ርሃብ' ምስል መደጋገምና የምንገነባቸው ግድቦች ለኢኮኖሚና ለስነምህዳር ቀውስ ምንጮች እንደሆኑ የሚነገሩን ወትዋች ዘገባዎች በውክልና 'የኔ ነው' ብለው በስፋት በማስነበብ። ከዚህ ጎን ለጎንም በልዩ ልዩ የፖለቲካ ጎራ የተሰለፉ የሃገራችን ፖለቲከኞች እንቅስቃሴ በመደገፍ ሆነ በመኮነን ብዙ ሃሳብ አንሸራሽረዋል። በዚህ መካከል ቁዋራቸው ቀላል የማይባሉ ወገኖች ጋዜጣዋና አዘጋጆችዋ አንዳንዴ ለገዥው ፓርቲ የለበጣ ሙገሳ እያሳዩ በተጨባጭ ወደ ጨለምተኝነትና ጽንፈኝነት እየነጎዱ መሆኑን ሲተቹ ለሎች ወገኖች ደግሞ በተቃውሞው ጎራ ዙርያ የተለያዩ ጌቶች መቀያየር(እንደ ፕሮፌሰር መስፍን አባባል 'አርባ አምባሻ መላስ') ሃሳብ በሂሳብ አወራራጅነታቸውን ከመንቀፍ አልቦዘኑም። እነዚህ መሰል አስተያየቶች ቢያከራክሩም (የጋዜጣዋና የታዛቢዎችዋ የተለያየ ሃሳብና አቋም የመግለጽ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ) የዋና አዘጋጆችዋ ወደውጭ ተመልካችነት፣የባእድ አጀንዳ አራማጅነትና ውጭ ተኪዶ 'በሚላስ አምባሻ' እና 'ስልጠና'( ወይም ትምህርት) ስራን የመከወን ፍላጎታቸው ሳይዛነፍ መቀጠሉ አሌ የሚባል አይደለም። ዋና አዘጋጆቹ ከሶስት ወራት በፊት ጀምሮ በማከታተል ወደ አሜሪካና ሌሎች ሃገሮች ለዚሁ ጉዳይ መሄድ መጀመራቸው አስረጂ ከመሆኑ በላይ ከሁሉም በጣም ቀድሞ የሄደውና እዚያ የከረመው አብይ በማያሻማ መልኩ ይህንን ገልጾታል።

አብይ ተክለማርያም ከአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ጋር ባደረገው ምልልስ የጋዜጣዋ መቆምና የአዘጋጆቹ 'መሰደድ' ዋናው ምክንያት 'አዲስ የመልቲ ሚድያ ስርዓቶችን በመጠቀም' እሱና ባልደረቦቹ ከውጭ ሁነው መንግስትን ለመጣል ካቀዱት ፕሮጀክት ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ይፋ አድርጓል። ይህ ደግሞ 'መንግስት ሊያስረን ስላሰበ ቀድመን አመለጥን' የሚለውን መከራከሪያ ከመጻረሩ በላይ 'በራሳቸው ምርጫ ቀደም ብለው ካገር እንደወጡ እንጂ ማንም እንዳላሳደዳቸው ከበቂ በላይ ይነግረናል። ከሁሉም በላይ አብይ በሰጠው ቃለመልልስ "የሃገራችንን አስከፊ ሁኔታ ይለውጣል ብየ በማስበው በማንኛውም ነገር ላይ እሳተፋለሁ" ብሏል። በመልቲ ሚድያ ግንባርም የሚከፍተው አዲስ ጦርነት እንዳለ ሲጠቁም ስለዝርዝሩ መናገር 'መንግስትን ማንቃት' እንዳይሆንበት በመቆጠብ ነበር። ይህ ደግሞ ውጭ ሃገር ሄደው በወል ለማከናወን ያሰቡት የፖለቲካ ዓላማ ጭምር ለማሳካት አቅደው ስለመሆኑ ምስክርነት ሰጥቶናል። ግልጽ አንድምታው "ማንኛውንም ዓይነት ትግል አካሂዳለሁ"(ትጥቅ ትግልን ለመግለጽ የዲያስፖራው ሽምቅ ተዋጊ የሚጠቀምበት ቋንቋ ልብ እንላለን) ከሚለው ጽንፈኛ ወገን ጋር ጉዟቸውን በማቀናጀት 'አንድ አምባሻን በደንብ መግመጥ' መሻታቸውና ለዚህም ሲሉ ፈቅደው ወደ ውጭ መሄዳቸውን ነው። ከነዚህ ተጨባጭ እውነቶች የምንደመድመው ደግሞ አዲስ ነገሮች በሰላማዊ የሃገራችን የፖለቲካ መድረክ በ'ነጻ ፕረስ' ሽፋን 'አርባ አምባሻ እየላሱ' የሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ተጠናቅቆ ውጭ ሂደውና 'አንድ አምባሻ እየገመጡ' ሰላማዊ ባልሆነው መድረክ ለመንቀሳቀስ እቅዳቸውን በቅደም ተከተል እያከናወኑ መሆኑን ነው። እናም ዞምቢዎቹ በ'አዲስ' ስም የጠሩትን አሮጌ ነገር አንዱን ምእራፍ ትተው ለቀሪው ምእራፍ በአዲስ ነገረኝነት ወደ ውጭ ሂደዋል።

<u>ሙሾውና ቁዘማው ካንጀት ወይስ ካንገት?</u>

በዞምቢዎቹ ጋዜጣ መቆምና 'የመሰደድ ዜና' ዙርያ በሃገራችን 'ነጻ' ፕሬሶች እየወጡ ያሉት ዘገባዎችም ሊቀሰቅሱት በሚጥሩት የአመል 'አቧራ' እየታዘብናቸው ነው። ሃሙስ ህዳር 24 ለጋዜጣዋ ቅርበት ባላቸው ሰዎች በኩል ወሬው ሲሰራጭ የማውቃቸው አምደኞችዋና ወሬውን በሰሙ ብዙ

አንባቢዎችዋ ዘንድ ከፍ ያለ ቅሬታ ስሰማ ነበር ። እጅግ በጣም ጥቂት ከሆኑት አስተያየት ሰጪዎች በስተቀር ብዙ ሰው በተለይ ለጋዜጣዋ ና ጋዜጠኞችዋ ቅርበት ከላቸው መካከል ውንጀላውን ያመነ ወገን አላጋጠመኝም። የብዙዎች ብስጭትም በማይረባ ሰበብ የጋዜጣዋ መቆም ለምን እንዳስፈለገና እዘጋጆቹ ‵እንዴት ለቪዛና ለስኮላረሰሽፕ ሲሉ″ ሃገር ጥለው መኮብለል እንደመረጡ ‵አዲስ ነገረኞች′ የምላቸው አድናቂዎቿ ሳይቀር በድራማው ሲያፍሩና ድርጊቱን ሲነቅፉ በመስማቴ ገርሞኝ ነበር። በተከታዩ ቀን በወጡት ጋዜጦች ዜናው ሲዘገብም እንዲሁ። ውጭ የሄዱት የአዲስ ነገር አዘጋጆች እርብ ምሽት ለቪኦኤ የሰጡት ቃለ ምልልስና የደህንነት መስሪያ ቤት መግለጫ ጎን ለጎን በቅዳሜና እሁድ ጋዜጦች ታትሞ ሲወጣም እውነትነቱን የተጠራጠረ ሰው አላጋጠመኝም። ማክሰኞ ለህትመት በበቁት ፕሬሶች ጉዳዩ መጠነኛ ‵የማሪጮህ ሽፋን′ ቢሰጠውም እንደሌሎች በግል ፕረሶች የሚዘገቡ ወቅታዊ ጉዳዮች የማደናገር አቅም ኑሮት ′በመንግስት ለእስራት ተፈልገው′ ስለመሰደዳቸው አንባቢን አላሳመነም።

ስለጉዳዩ በእለቱ የታየው አዘጋገብም ከትዝብት ርቆ ለማያውቀው ‵ነጻ′ ፕረሳችን ለተጨማሪ ሃፍረት የዳረጉ ነገሮችም ተስተውለዋል። የ′አዲሰ ነገር በመንግስት መፈለግና መሰደድ′ በአዘጋጆቿ ውጥን ተዋንያን ከሆኑ ጥቂቶች በስተቀር ማንንም እንዳላሳመነ እየታውቀና በጉዳዩ ብዛት ያላቸው አንባቢዎችም ሆኑ ‵የቅርብ ሰዎች′ የሚሉት የተለየ ነገር እንዳለ በግልጽ እየታወቀ አንዳችም ሽፋን አለማግኘቱ ‵ነጻው ፕረስ′ ራሱን ነጻ ያላወጣና የነጻ ሃሳብ ጸር መሆኑ በግልጽ ይመሰክራል። የተዘገበውም ለወዶ ኮብላዮቹ ሽፋን ሰጭ ሊሆን የታሰበ ‵ በፕሬስ ነጻነት ላይ የተደረገ አፈና′ አስመስሎ ‵አቧራ የማጨስ′ ሙከራና ሟች አድናቂ ከሆነው ባህል የተወረሰ ትዝታዊ ‵የእንዲህ ነበሩ′ እንጉርጉሮ ብቻ ነበር። አመል ሁኖባቸው እንጂ ፕሬሶቹ ጉዳዩ እነሱንም እንዳላሳመነ መረዳት አይከብድም። ዜናውን በማሰራጨትና ‵የሟችን አንገት ማስረዘም′ ላይ ከአንጀት የሚመስል ሽፋን ቢሰጡም ስለ ስሞታው ዋና ጭብጥ ግን ‵ከአንገት′ ያለፈ ተሙዋጋችነት አንዳችም አልወጣቸውም። ከአንጀት የመቆርቆር ተውኔቱን የመራችው አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ስትሆን ‵የሃዘን′ እትም በማውጣት ለጉዳዩ ሙሉ ሽፋን ስትሰጥም ‵አዲስ ነገር ስትታጣ′ ጩኸት ባለመበርከቱ በመቆጨት ስለጉዳዩ ለምን በርእሰአንቀጽ አልጻፉም ወዳለቻቸው ፕሬሶች ጣት ቀስራለች። ሌላው ቀርቶ አውራምባ ታይምስ ከልብ ለማስመሰል ሙሾ በደረደረችበት የሃዘን እትም ውስጥ ተሽኮርምማ የወጣች አንዲት ዜና ለጉዳዩ ስላቃዊ ይዘት ስላላትና የ′ነጻው ፕረስ′ የእርስበርስ ይሉኝታ ስለማይፈቅድ ‵አይናፋር′ ሁና መቅረብ የግድ ሁኖባታል። በጋዜጣዋ የውስጥ ዜና ገጽ በታችኛው የግራ ጠርዝ የተጻፈችው አይናፋሯ ዜና ‶የአውራምባ ታይምስ አዘጋጆች ትናንት ዛሬና ነገ በተከታታይ ፍ/ቤት ይቀርባሉ″ ትላለች። ይህች ዜና ጋዜጣዋ ከአንገት የአጋርነት ሙሾ ለምታውርድላችው ዞምቢዎች ሽርዳጅና ‵ክስ ሊመሰረትብን ሲል አገር ጥለን ጠፋን′ ለሚል ሙግታቸው ፍጹም አፍራሽ በመሆኑዋ ጥግ እንድትቀመጥ ተደርጋለች። ሙሉ የሃዘን ሽፋን በሰጠችው ‵የአዲስ ነገር መታጣት′ ሙሾ ውስጥ ይህች የአንጀት ዜና የ′ነጻው′ ፕረስ ወግ እና ‵ተገቢ አመል′ እንዳታበላሽ ታሰቦባት እንጂ ‵እኛ ችለነው ስራ ያልተውንበት ነገር እሷን ማስፈርጠጡ የማይመስል ነገር″ በሚመስል የየዋህ ባልቴት የአፍ ወለምታ ልቅሶ ቤት ውስጥ ልታስቀን እንዳልከጀለች እንግምት። ከዚህ የምንረዳው ሙሾ አውራጆቹ ፕሬሶችም ተቃውሞን እንደ ስራ ዘርፍ በሚቆጥር አመል በይሉኝታ ወይም ሆን ተብሎ በ′እከኪልኝ ልከክልሽ′ ና ″አምባሻ መላስ″ ራሳቸው ጭምር የማያምኑበትን ክስ ሰፊ ሽፋን ሰጥተው እውነት እንደሆነ ሊያሳምኑን መድከማቸውን ነው። ዞምቢዎቹ ከአለማቀፍ ‵ተሟጋች′ ሃይሎችና ከዲያስፖራ ጽንፈኞች ለሚገኝ ‵አምባሻ′ ሲባል ዲሞክራሲያዊ ስርዓታችንና የሃገራችን ደህንነት ለግል ጥቅም ለውጠው ፈቅደው ሲሰደዱ እንዲህ አይነቱ የፕረሶችና የተቃዋሚዎች ግብዝነት ከጎናቸው እንደማይለይ ተማምነው ነው ብንል ስህተት አይመስለኝም።